ብርሃን ባንክ
Berhan Bank

# የብርሃን ባንክ አክስዮን ማህበር
# የባለአክስዮኖች 16ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ የጉባኤ ጥሪ

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የንግድ ሕግ አንቀጽ 366(1)፣367(1) እና 370 እንዲሁም በአክስዮን ማህበሩ መመስረቻ ጽሁፍ 17(1) መሰረት የብርሃን ባንክ አክስዮን ማህበር የባለአክስዮኖች 16ኛ ዓመታዊ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ለጥቅምት 18 ቀን 2018 ከጠዋቱ 2:00 ሰዓት ጀምሮ አዲስ አበባ ቦሌ በሚገኘው ሚሊኒየም አዳራሽ ይካሔዳል። በመሆኑም የተከበራችሁ ባለአክስዮኖች በዕለቱ በጉባኤው ላይ እንድትገኙልን የዳይሬክተሮች ቦርድ ጥሪውን ያስተላልፋል።

## 1. ማህበሩን የሚመለከቱ ዋና ዋና መረጃዎች

1.1 የአክስዮን ማህበሩ ዋና መሥሪያ ቤት አድራሻ አዲስ አበባ፤ ቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 3 የቤት ቁጥር 2185፤ ድረ-ገጽ www.berhanbanksc.com

1.2 የአክስዮን ማህበሩ የምዝገባ ቁጥር = 06/1/28428/01

1.3 የአክስዮን ማህበሩ የተፈረመ ዋና ገንዘብ/ካፒታል/= 4,534,930,000.00

1.4 የአክስዮን ማህበሩ የተከፈለ ዋና ገንዘብ/ካፒታል/= 4,534,930,000.00

## 2. የ16ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ አጀንዳዎች

2.1 አጀንዳውን ማጽደቅ፤

2.2 የተከናወኑ የአክስዮን ዝውውሮችን ማጽደቅና አዳዲስ ባለአክስዮኖችን መቀበል፤

2.3 የዳይሬክተሮች ቦርድን እ.ኤ.አ. የ2024/25 ዓመታዊ ሪፖርት ማዳመጥ፤

2.4 የውጭ ኦዲተሮችን እ.ኤ.አ. የ2024/25 ዓመታዊ የኦዲት ሪፖርት ማዳመጥ ፤

2.5 ከዚህ በላይ በቀረቡት ሪፖርቶች ላይ ተወያይቶ መወሰን፤

2.6 የዳይሬክተሮች ቦርድ የጥቆማ እና የምርጫ አፈጻጸም ፖሊሲ እና መመሪያ ተወያይቶ ማጽደቅ

2.7 በዘመኑ የተጣራ ትርፍ አደላደል እና አከፋፈል ላይ ተወያይቶ መወሰን፤

2.8 የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን ወርኃዊ አበልና ዓመታዊ ክፍያ መወሰን፣

## 3. ማሳሰቢያ

3.1 በጉባኤው ላይ ለመገኘት የማይችሉ ባለአክሲዮኖች በንግድ ሕግ አንቀጽ 377 መሰረት ጉባኤው ከሚካሄድበት ቀን አስቀድሞ ባሉት ቀናት ውስጥ በአዲስ አበባ ከተማ፤ ቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 3 የቤት ቁጥር 2185 በሆነውና ቦሌ ድልድይ ፊት ለፊት በሚገኘው የባንኩ ዋና መስሪያ ቤት የአክስዮን አስተዳደር ክፍል በመገኘት የውክልና ፎርም/ቅጽ በመሙላት ተወካይ በመወከል ወይም፤ በስብሰባው ለመገኘትና ድምጽ ለመስጠት የሚያስችል የውክልና ማስረጃ ያለው ተወካይ ዋናውን እና አንድ ፎቶ ኮፒ በጉባኤው ዕለት ይዞ እንዲቀርብ በማድረግ በወኪሎቻቸው አማካይነት መሳተፍ የሚችሉ መሆኑን በአክብሮት እንገልጻለን። ሆኖም አንድ ባለአክስዮን መወከል የሚችለው አንድ ተወካይ ብቻ መሆኑን እንገልጻለን።

3.2 የአክስዮን ማህበሩ ባለአክስዮኖች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በጉባኤው ላይ ለመሳተፍ በሚመጡበት ጊዜ ኢትዮጵያዊ ዜግነታቸውን የሚያሳይ ብሔራዊ መታወቂያ ወይም የፋይዳ መታወቂያ ቁጥር(National ID Number) የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ወይም መንጃ ፍቃድ ዋናውንና ኮፒ መያዝ አለባቸው። እንዲሁም ትውልደ ኢትዮጵያውን የውጭ አገር ዜግነት ያላቸው የማህበሩ ባለአክስዮኖች ትውልደ ኢትዮጵያዊ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ቀኑ ያላለፈበት የትውልደ ኢትዮጵያ መታወቂያ ካርድ ይዘው መቅረብ እንዳለባቸው በአክብሮት እናሳውቃለን።

3.3 የባንኩን እ.ኤ.አ. የ2024/25 ዓመታዊ ሪፖርትና የዳይሬክተሮች ቦርድ የጥቆማ እና የምርጫ አፈጻጸም ፖሊሲ እና መመሪያ ከባንኩ ድረ-ገጽ ላይ ማግኘት ወይም አክስዮን አስተዳደር ክፍል በመቅረብ መውሰድ የምትችሉ መሆኑን እንገልጻለን።

**የብርሃን ባንክ አ.ማ**
**የዳይሬክተሮች ቦርድ**